
ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በኢን ላይን ፈተና ዙሪያ የተሰጠ ኦረንቴሽን

የፈተናዉ አሰጣጥ

- ፈተናዉ በአን ላይን ይሰጣል
- ፈተናዉ በትም/ቤታችን ይሰጣል
- ተማሪዎች በዙር የሚፈተኑ ይሆናል

የኦንላይን ፈተና ያለዉ ጠቀሜታ



ቅድመ ዝግጅት

- በየመፈተኛ ጣቢያችሁ ተለይቶ ወደተቀመጠው መፈተኛ URL ትገባለችሁ።
- ከገባችሁ በኋላ ከትምህርት ቤታችሁ የተሰጣችሁን መለያ ቁጥርና የሚስጥር ቁጥር User Name እና Password በማስገባት login የሚለውን መጫን።

የቀጠለ . . .

- ወደቀጣዩ ገጽ ስትገቡ ፓስወርድ ቀይሩ የሚል መልዕክት ይነበባል። ስለሆነም Current password የሚለው ላይ ከትምህርት ቤታችሁ የተሰጣችሁን በማስገባት New password የሚለው ላይ አዲስና የማትረሱትን 8 ካራክተሮችን የያዘ የሚስጥር ቁጥር በማስገባት ትቀይራለችሁ። ይህ አዲሱ ፓስወርድ ከዚህ በኋላ ወደዚህ ገጽ የምትገቡበት አዲስ መግቢያ ይሆናችኋል ማለት ነው።

የቀጠለ . . .

- አዲስ የቀየራችሁትን ፓስወርድ Save changes የሚለውን በመጫን ከጨረሳችሁ በኋላ Continue የሚለውን በመጫን ወደ ቀጣዩ ገጽ ትገባላችሁ።
- እዚህ ጋር የምትወስዱትን የፈተና አይነት ታያላችሁ። ከዚያም የፈተናው ስም ላይ click አድርጋችሁ ስትገቡ ቀጥታ ወደፈተናው ይወስዳችኋል።

የቀጠለ . . .

- እዚያው ገጽ ላይ Attempt Exam የሚለውን በመጫን በመፈተኛ ቦታችሁ በፈታኞቻችሁ የሚነገረውን የፈተና መለያ ቁጥር Quiz password የሚለው ላይ ታስገቡና start attempt የሚለውን በመጫን ጥያቄዎቹን ወደምታገኙበት ገጽ ይመራችኋል።

የቀጠለ . . .

በዚህ ገጽ

- በስተግራ በኩል የፈተናውን አይነት፣
- መሃል ላይ ከላይ የተፈታኞች ሙሉ መረጃ፣
- መሃል ላይ ከታች፣ ጥያቄዎችና ጥያቄውን ሰርቶ ለማጠናቀቅ የቀራችሁን ደቂቃ መቁጠሪያ እንዲሁም
- በቀኝ በኩል የተመልሱና ያልተመልሱ ጥያቄዎች መለያ (exam overview) ታገኛላችሁ።

የቀጠለ . . .

- መሃል ላይ በአንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ ብቻ ከሚያሳየው ቦታ ጥያቄውን በአግባቡ አንብባችሁ መልሱን ከመረጣችሁ በኋላ Next page የሚለውን በመጫን ወደቀጣይ ጥያቄ ማለፍ ትችላላችሁ።
- አንድ ጊዜ የመረጣችሁትን መልስ መቀየር ከፈለጋችሁ ከእያንዳንዱ መልስ የተሰጠው ጥያቄ ስር የሚመጣውን Clear my choice የሚለውን click በማድረግ የመጀመሪያውን ማጥፋትና አዲሱን መልስ መምረጥ ይቻላል።

የቀጠለ . . .

- መልሱን ከመረጥን በኃላ ደግሞ ተመልሰን በድጋሚ ልናየው የምንፈልግ ከሆነ ከጥያቄው በስተግራ ባለው ቦክስ ያለችውን flag question የሚለውን click በማድረግ ጥያቄውን ተመልሳችሁ ለማየት ምልክት አድርጋችሁ ማለፍ ትችላላችሁ።

የቀጠለ . . .

- ምልክት ለማድረጋችሁም በስተቀኝ በኩል ያለው የጥያቄዎችን መመለስ አለመመለሳቸውን የሚያሳየው Exam overview ላይ ጫፉ ቀይ ምልክት ኖሮበት ታገኙታላችሁ።

እዚህ ቦታ

- መልስ የተሰጠባቸው ጥቁር ምልክት ሲኖራቸው
- መልስ ያልተሰጠባቸው ነጭ እና
- ድጋሚ አየዋለሁ በሚል flag question የተደረጉት ቀይ ምልክት ሆኖባቸው በቀላሉ እንዲለዩ ሆነው ይታያሉ።

የቀጠለ . . .

- ሁሉንም ጥያቄዎች ሰርታችሁ ስትጨርሱ Finish attempt የሚለውን ስትጫኑ የጥያቄዎቹን ቁጥር በመዘርዘር የሰራችሁትንና ያልሰራችሁትን ለይቶ ያሳያችኋል። የተመለሰውን: Answer saved ብሎ ሲያስቀምጥ ያልተመለሰውን: ፣Not yet answered ብሎ ከጥያቄው ፊት ያስቀምጣል።

የቀጠለ . . .

- እዚህ ጋር ያልመለሳችሁትን ጥያቄ ለመስራት Not yet answered ከሚለው ጽሁፍ ፊት ለፊት ያለውን ቁጥር በመጫን ወይም በስተቀኝ (exam overview) ጋር በመሄድ Not yet answered የተባለውን ጥያቄ ቁጥር በመጫን ወደጥያቄው ተመልሶ በመግባት መስራት ይቻላል።

የቀጠለ . . .

- ሁሉንም ጥያቄዎች ከመለሳችሁ በኋላ እዛው ገጽ ላይ በስተቀኝ በኩል **exam overview** የሚለው ጋር በመምጣት ከስሩ ያለውን **Finish attempt** የሚለውን ክሊክ በማድረግ በድጋሚ የተመለሱና ያልተመለሱ ጥያቄዎች ወደሚታዩበት ገጽ ይመራናል።

የቀጠለ . . .

- መጨረሳችንን እርግጠኛ ስንሆን እዚሁ ገጽ ላይ ከታች ያለውን Submit all and finish የሚለውን እንጫናለን። Confirmation የምትል box ላይ እርግጠኛ ናችሁ፣ ጨርሳችኋል የሚል ማረጋገጫ ጥያቄ ታያለችሁ። ያኔ ድጋሚ Submit all and finish የሚለውን በመጫን ታጠናቅቃለችሁ።
- ካረጋገጣችሁና Submit all and Finish የሚለውን ከተጫናችሁ በኋላ ወደዋናው ገጽ ይመልሳችኋል። እዚህ ጋር የፈተናችሁን Status ማየት ይቻላል።

የቀጠለ . . .

- እዚህ ጋር ፈተናውን ስለጨረሳችሁ finished የሚል ጽሁፍና የተፈተናችሁበት ቀን እና የጨረሳችሁበት ሰዓት ተመዝግቦ ታያለችሁ።
- እሁን ፈተናውን ስለጨረሳችሁ በቀኝ በኩል ጠርዝ ላይ ስማችሁ ያለበት ጋር click በማድረግ Logout በማድረግ ከገጹ መውጣት ይገባል።


thank you